# የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄን (አብን) የድጋፍ ዘመቻ ይቀላቀሉ!

welkait.com/

**የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን ) National Movement of Amhara (NAMA) የድጋፍ ዘመቻ ይቀላቀሉ!**
**(Dessalegn Chanie Dagnew NAMA Chairman)**




በአማራ ህዝብ ላይ ባለፉት አመታት የተፈፀመውን የጥፋት ሴራ ከስሩ በመንቀልና የተቃጣበትን ዘርፈ ብዙ ጥቃት ለመቀልበስ ህዝባችን ከአጥናፍ አጥናፍ ተነስቷል። አማራነት ዛሬ ከፍታ ላይ ነው።

የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) መመስረት የአማራን ህዝብ ሁለንተናዊ የህልውና ትግል ድርጅታዊ ቅርፅ ያላበሰ ሲሆን ለሲቪክ አደረጃጀቶችም መነቃቃትን የፈጠረ ሂደት ነው። አብን ለአማራ ህዝብ ከፍተኛ ተስፋና የትግል መነቃቃትን ፈጥሯል። የአማራ ህዝብ ፍላጎቶቹንና

ጥቅሞቹን ለማስከበር በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደ አንድ ልብ መካሪ ፣ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆኖ መቆሙ ያስተማረን ነገር ቢኖር በአማራነታችን በአግባቡ ከተደራጀን የህዝባችን ድል ቅርብ እንደሆነ ነው።

ባለፋት ወራት በአብን የተሰሩ ህዝባችንን የማንቃት ስራዎቻችን አይን ከፋች ነበሩ። ሰፊው ህዝባችን አማራን አቅመ ቢስ ያደረገውን ፣ ሲቀጠቀጥበትና ዋጋ ሲከፍልበት የነበረውን አክሳሪና በተግባር ተሞክሮ የከሸፈውን ሃሳዊ “የዜግነት” ፖለቲካ ላይ ተቸንካሪነቱን ትቷል።

ነገር ግን ዛሬም ከአማራ ህዝብ ጀርባ ወርደው መቆም የማይችሉት የፓለቲካ ጅምላ ነጋዴዎች የድጋፍ መሰረታቸውን ቢያጡም በገንዘብና በፕሮፓጋንዳ አቅማቸው የደለቡ ስለሆኑ የአማራን ህዝብ የህልውና ትግል የመነተት አቅማቸው ገና አልተዳከመም። ትግላችንም እስከ ድል ደጃፎች መሆን ይገባዋል።

ከፊታችን ላለው ድል ህዝባችንን በተከታታይ ማስተማር ፣ ማንቃት ፣ ማደራጀት ፣ መሰብሰብና ማታገል ፤ ፀረ-አማራነታቸውን ማስጣል ፤ ሃሳዊ የዜግነት ፖለቲካ ትርክታቸው የአማራን ህዝብ ጥያቄዎች ከማድበስበስ በዘለለ አንዱን እንኳን ማስመለስ እንደማይችል ማስገንዘብ ይገባናል። ጥንፈኛ የብሄር ድርጅቶች ቀን ከሌት የአማራ የሆነን ነገር ሁሉ ለማጥፋት እየሰሩ ባለበት በአሁኑ ጊዜ አማራዊ አደረጃጀቶችን እንድንጥል የሚሰሩት ስራ ለአማራ አክሳሪና አጥፊ እንደሆነ ለማሳየት አብን ሰፊ የፖለቲካ ስራ እየሰራ ነው።

ይህንን ስራ አጠናክሮ ይቀጥል ዘንድ የእያንዳንዱን አማራ የገንዘብ ድጋፍ ይሻል። እስከአሁን የህዝባችን ጠንካራ ድጋፍ በመኖሩ ብቻ በመደበኛ መንገድ ሰፊ ገንዘብ ሳናሰባስብ ብዙ ስራዎችን ሰርተናል። በቀጣይ ለታቀዱና ለሚከናወኑ ስራዎቻችን የአማራን ህዝብ ድጋፍ በተደራጀ መንገድ እንፈልጋለን።

የአባልነትና ወርሃዊ መዋጮ እንክፈል ፣ ልገሳ እናድርግ ፤ ድጋፍ እናስተባብር ፣ በፋይናንስ የተጠናከረ የአማራ ድርጅት እንፍጠር።

አንድ አማራ ለሁሉም አማራ ፣ ሁሉም አማራ ለአንድ አማራ !